የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 46
ADDIS ABABA, 22th May, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹/፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኦስትሪያ ፌደራል መንግስት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……...................ገጽ ፲፰ሺ፬፻፶፭

**Content**

Proclamation No. 1380/2025

The Air Transport Agreement Concluded Between the Government Of The Federal Democratic Republic Of Ethiopia And The Austrian Federal Government Ratification Proclamation Page………….. ........ 18455

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹/፪ሺ፲፯**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኦስትሪያ ፌደራል መንግስት መካከል የተፈረመውን የአየር ትራንስፖርት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኦስትሪያ ፌደራል መንግስት መካከል የአየር ትራንስፖርት ስምምነት፤ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ባካሄደዉ ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

**Proclamation No. 1380/2025**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT AGREEMENT SIGNED BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AUSTRIAN FEDERAL GOVERNMENT**

**WHEREAS**, the Air Transport Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Austrian Federal Government was signed on 5th of November, 2020;

**WHEREAS,** the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 13th day of May 2025;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኦስትሪያ ፌደራል መንግስት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኦስትሪያ ፌደራል መንግስት መካከል እ.ኤ.አ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የአየር ትራንስፖርት ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

፫. **አስፈጻሚ አካል**

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዘዳንት**

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Air Transport Agreement Concluded between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Austrian Federal Government Ratification Proclamation No 1380/2025".

2. **Ratification of the Agreement**

The Air Transport Agreement Concluded between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Austrian Federal Government signed at Addis Ababa in October on the 26th day of 2013, is hereby ratified.

3. **Implementing Organ**

The Ethiopian Civil Aviation Authority is hereby empowered to implement this Agreement.

4. **Effective Date**

This proclamation shall come in to force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 22th day of May, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**